# ግልጽ ደብዳቤ
# ለኢሕአዴግ ከፍተኛ የአመራር አባላት

ግርማ ካሣ (ቺካጎ)
muzIky68@yahoo.com

ግንቦት 1 ቀን 2001

ውድ ኢትዮጵያዊ ወንድሞቼ፡

በቅድሚያ «የእግዚአብሔር ሰላምና ጸጋ ከናንተና ከቤተሰቦቻቹህ ጋር ይሁን» በማለት የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ።

አላማዬ አንድ እና አንድ ናት። ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም ሰፍኖ፣ ሁላችንም ተከባብረንና ተፋቅረን እንደ አንድ ሕዝብ ተያይዘን እንድንኖር ። እናንተ ገዛቹህ፣ ሌላው ገዛ ፣ ቁም ነገሩ «ማነው የሚገዛው? » የሚለው ላይ አይደለም። ማንም ገዛ ማንም፣ ቁም ነገሩ «አገር ሰላም ሆና፣ የዜጎቿ መብት ተጠብቆና ተከብሮ፣ ድህነት ተቀርፎ፣ ኢትዮጵያዊያን ቢያንስ ቢያንስ በልተው ያድራሉ ወይ? » የሚለው ነው።

እውነቱን አልደብቃችሁም። ደጋፊያችሁ አይደለሁም። የምታራምዱት በዘር ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ አይጥመኝም። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው አምባገነን ባህሪያችሁን ልቀበለው አልችልም። ስለሆነም ባለኝ አቅምና ጉልበት ሁሉ ተቃውሞዬን አሰምቻለሁ።

በዚህ ጽሁፌ ግን ወገዛና ቁጣ ይዤ አልመጣሁም። እናንተን ለማዋረድ፣ ለመክሰስና ለማቅለል አሁን ፍላግት የለኝም። ነገር ግን የልቤን የውስጤን ላጋራቹህ፣ በስራቹህ ሳይሆን በስብእናቹህና በኢትዮጵያዊ ወንድምነታችሁ አክብሪያችሁ፣ ከናንተ ጋር ሃሳብ ለለዋወጥ ይሄንን ጽፌያለሁ።

ከ 130 ቀናት በፊት እህቴና እህታቹህ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በአሥር ፖሊሶች እየተገፋች ወደ ቃሊቲ ወረደች። እስከአሁን ድረስ በጨለማ ቤት ውስጥ ተቀምጣለች። የ78 አመቱ ሽማግሌ የናንትም የኔም አባት የሚሆኑ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም በሰደፍ ተደበደቡ።

ይህንን አሳዝኝ ዜና ስሰማ ውስጤ በጣም ቆሰለ። «እኛ ኢትዮጵያውያንን ምንድን ነው የነካን? ምንድን ነው እንደዚህ አወሬ የሚያደርገን ? » ብዬ በትካዜና በቁጣ ተሞላሁ።

ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወራት እየቆጠርን መጣን። ችግሩ እየባሰና እየተወሳሰበ ሄደ። አሁንም «ከሰላምና ከእርቅ ውጭ ሌላ አማራጭ አይበጅም» የሚል ጠንካራ

እምነት ስላለኝ፣ የአገር ሽማግሌዎች ሰብሳቢ የሆኑት ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይሳዕቅን በስልክ አነጋገርኳቸዉ። « በተፈጠረዉ ነገር በጣም አዝነናል። ይፋ ወጥተን አልተናገርንም እንጂ ዉስጥ ዉስጡን ወ/ት ብርቱካን እንድትፈታ ብዙ ጥረት እያደረግን ነዉ። እኔ እንደዉም ብዙ ጊዜ ይሄ ነገር እያስጨነቀኝ እንቅልፍ ሁሉ የለኝም» አሉኝ።

«ታዲያ ቢያንስ ቢያንስ ለምንድን ነዉ ሽምጋሌዎች ቃሊቲ ድረስ ሄደዉ ወ/ት ብርቱካንን የማይጠይቋት? ያላችበትንስ ሁኔታ ለምን አያሳወቁንም?» ብዬ ጠየኩኝ። ፕሮፌሰሩ በቅርብ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚሄዱና የተቻላቸዉን እንደሚያደርጉ፣ የመንግስት ባለሥልጣናትንም እንደሚያነጋግሩ ነገሩኝ። ወ/ት ብርቱካን መፈታት እንዳለባትንና ለሁላችንም የሚበጀዉ ሰላም እንደሆነ ተማምነን ፣ እኔም ጥረታቸዉን እንደማከብር ገልጬላቸዉና አመስግኛቸዉ ተለያየን።

ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይሳዕቅና ሌሎች ሽማግሌዎች ሚያዚያ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በሼራተን ሆቴል ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጡ። ከመግለጫዉ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ከማስፈታት ሽማግሌዎቹ ያደረጉት ጥረት ብዙ እንዳልተሳካላቸዉ ለመረዳት ቻልኩ። ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይሳዕቅም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ፊት ለፊት ሳያናግሩ ባዷቸዉን ወደ አሜሪካ ሊመለሱ እንደሆነ ተረዳሁ።

የሽምግልናዉ ጥረቱ መሄድ ያለበትን ያህል መሄድ አልቻለም። ሃዘኔ እየጨመረ መጣ። ለሁላችንም ወደ ሚበጅ መንገድ እየመጣን እንዳልሆነ ገባኝ። በጣም እየተራራቅ እንደሆነ አስተዋልኩ። አይኖቼ ተስፋ የሚሰጥ ብርሃን ማየት ተሳናቸዉ።

እናንተ የኢሕዴግ ባለሥልጣናት፣ ለሃያ ወራት አስራቸሃትም «ጠላቶቼ አይደሉም» ያለችዉ፣ በአገር ዉስጥ ሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ የምትታገለዉ፣ በሕግ የተመዘገበ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር የሆነችዉ፣ በቤቷ ቦምብና ፈንጂ ያልተገኘባት፣ በአገር ሽምግልናና ወግ መሰረት መንግስትንና ሕዝብን ይቅርታ እንደጠየቀች አለመካዷን «ቃሌ» በሚለዉ ጽሁፏ በገሃድ ያረጋገጠችዉ፣ የሰባ አራት አመት አሮጊት እናት ጧሪና የአራት አመት ሕጻን ልጅ እናት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ከመታሰር አልፎ በግፍ ይሄን ያህል ጊዜ በጨለማ ቤት ዉስጥ ስትቀመጥ ስመለከት፣ በሰላማዊ ትግል ላይ ትልቅ አደጋ እንደተፈጠረና ወደኋላ እየተመለስን እንደሆነ ገባኝ።

ያ ብቻ አይደለም። በቅርቡ የሰማኒያ አመት ሽምግሌ የሆኑትን አቶ ጽጌን ጨምሮ በርካታ ዜጎችን «ሽብርተኛ» በሚል ክስ እንደታሰሩም ሰምተናል።

«ሰላማዊና ሰላማዊ ትግል ብቻ» በሚል አርዕስት የሪፖርተር ጋዜጣ የትጥቅ ትግል እንደማያዋጣ ሪዕቡ ሚያዚያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም ባወጣዉ እትሙ ላይ ዘግቧል። ሪፖርተር ያለ ምክንያት ይህንን አርዕስት በኢዲቶሪያሉ ላይ ትኩረት

ሰጥቶት አላተመዉም። የአስተሳሰብ ለዉጥ (Shift) እየመጣ እንደሆነ ስለተረዳ ይመስለኛል።

አንድ የምወደዉና የማከብረዉ አባይ ሚዲያ የተሰኘዉ ድህረ ገጽ «የኢትዮጵያ ሰላማዊ ትግል» የሚል የተጻፈበት የመቃብር ሃዉልት ያለበት ምስል ለጥፎ አየሁ። ከምስሉ በታችም « The death of Peaceful Struggle in Ethiopia » የሚል አነበብኩኝ። ማመን አቅቶኝ አይኖቼን አሸሁ።

አባይ ሚዲያ የሰላማዊ ትግል ሞቷል ወደ ሚል መደምደሚያ እንዲሁ አልደረሰም። አባይ ሚዲያ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት የሰላማዊ ትግል ያራምዱ የነበሩ፣ አሁን በሰላማዊ ትግል ተስፋ ቆርጠዉ ወደ ማይፈልጉትና ከዚህ በፊት ወደ ሚቃወሙት የትግል አቅጣጫ እየሄዱ የመጡ ዜጎቻችን ጥቂቶች አይደሉም። ብረት ወደ ማንሳት እጆቻቸዉን የዘረጉ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸዉ እየጨመረ ነዉ። ይህ አካሄድ እጅግ አስፈራኝ።

ብረት ያነሱትን እናንተ «ሽብርተኞች» ብላቹህ ልትጠሯቸዉ ትችሉ ይሆናል። ነገር ግን እንናተ ጫካ የነበራቹህ ጊዜ ምን ትባሉ እንደነበረ ማስታወስ አለባቹህ እላለሁ። ጠመንጃ ያነሱ ወገኖች፣ ጠመንጃ ያነሱት፣ ክብራቸዉን ለመጠበቅና «በሰላም የመታገል እድል ተዘግቷል» ወደ ሚል ድምዳሜ ስለደረሱ ነዉ። ሰዉን እየገፋችሁት ወደ ማይፈለገዉ ደረጃ እያደረሳችሁት ያላችሁት፣ አውቃችሁም ሆነ ሳታወቁት፣ እናንተዉ ናቹህ እላለሁ።

የወደፊቱን አላዉቅም እንጂ፣ በአሁኑ ወቅት እናንተን በኃይል ገልብጦ ሊተካ የሚችል የተደራጀና የታጠቀ የተቃዋሚ ኃያል ይኖራል ብዬ አላስብም። አምናለሁ ዉትድርናን በመተመከከተ ጠንክራ ናቹህ። ምናልባት በዚህም ምክንይት «ምንም አንሆንም» ብላቹህ የመረጋጋት ሁኔታ ይታይባቹህ ይሆናል።

ነገር ግን በጣት የሚቆጥሩ ጥቂት ሰዎች ከመረሩና «እናጥፋ» ብለዉ ከተነሱ፣ ትልቅ ጥፋት ሊያደርሱ እንደሚችሉ የምትዘነጉት አይመስለኝም። እናንተም ትገድላላቹህ፣ እናንተም ትገደላላቹህ። እርስ በርስ መተላለቅ፣ መንገዶቻችን በደም መርጨት ይሆናል እጣ ፈንታችን። አንዴ ብጥብጡ ከተጀመረ ደግሞ በቀላሉ ማቆሚያ አያገኝም። የተዳፈነዉ ሁሉ ፈንድቶ ያኔ “ዋይ ዋይ ይሆናል»። ታዲያ ይሄንን ነዉ የምትፈልጉት ? ለዘመናት የነበረን የደም ታሪካችን እንዲቀጥል ነዉ አላማችሁ?

ከናንተ ዉስጥ አንዳንዶቻቹህ «ምን ያስፈራራናል? » ልትሉኝ ትችላላችሁ። አስተዋይ ከሆናቹህ ግን የምለዉ ይገባቹሃል ብዬ አስባለሁ። ደርግ ከአፍሪካ ትልቁ ጦር እንደነበረዉና እናንተ ከየት ተነስታቹህ የት እንደደረሳቹህ ካስታወሳቹህ እኔ ከምለዉ ጋር የምትስማሙ ይመስለኛል።

አዎ ፣ ሌላ ነገር ቢሆን ተስፋ ቆርጬ ሁሉንም ነገር ትቼዉ እቀመጥ ነበር። ነገር ግን በሰላምና በአገር ጉዳይ ላይ ምንጊዜም ተስፋ ሊቆረጥ አይገባም። ስለዚህ

የመሳካት እድሉ ከመቶ አንድ ያነሰ ቢሆንም፣ እስከመጨረሻዉ ድረስ እጓዛለሁ። ምናልባት ከኔና ከመሰሎቼ ለሚቀርበዉ ወንድማዊ የሰላምና የእርቅ የአሥራ አንደኛዉ ሰዓት ጥሪ፣ እግዚአብሄር ረድቷቹህ ፊታችሁን መለስ ታደርጉ ይሆናል በሚል፣ ይሄንን ጽፊያለሁ።

አሁን ያለዉን አስፈሪ የፖለቲካ አዝማሚያ ለመቀየር የሚረዳ፣ ሁላችንን ወደ መልካሙ መንገድ ወደ አንድነትና ወደ መከባበር የሚያመጣ፣ በሰለማዊ ትግል ያለንን እምነት የበለጠ የሚያሳድግልንን፣ ከፍቷቸዉና ተስፋ ቆርጠዉ ወደ ማይፈልጉት አቅጣጫ የሄዱትን ወንድሞቻችን አሳምነን ወደ ሰላሙ መንገድ ለማምጣት አቅም የሚሰጠንን፣ ጠቃሚ እርምጃዎች ከናንተ እናይ ዘንድ ይሄንም ጽፊያልሁ። ኳሷ በናንተ ሜዳ ዉስጥ ነዉ ያለችዉ።

ስለሆነም በኢትዮጵያዊ ጨዋነትና በአክብሮት የሚከተሉትን ተጨባጭ እርምጃዎች እንድትወስዱ ምክሬንና ተማጽኖዮን አቀርባለሁ።

- እህቴና እህታቹህ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ መኖሪያዉ ቃሊቲ ሳይሆን ፈረንሳይ ለጋሲዮን ነዉ። ስለሆነም ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ፣ ባስችኳይ፣ አሁን መፈታት አለባት። የርሷ መታሰር እናንተንም እኛንም ማንንም አይጠቅምም። ስህተት ሰርታችሁዋል። ስህተታችሁን ተቀበሉና ስህተታችሁን አርሙ።

- ግንቦት ሰባት፣ ኦነግ፣ የአርበኛች ግንባር ... እያላቹህ ሰላማዊ ዜጎችን ማፈንና ማሰር አቁሙ። ቢቻል ከታጠቁ ድርጅቶች ጋር የተኩስ አቁም ስምምነት አድርጋቹህ ችግሮች በሰላም የሚፈቱበትን ሁኔታ አመቻቹ።እልህ ዉስጥ አትግቡ።

- የፊታችን የ2002 ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ እንዲሆን፣ የፖለቲካ ምህዳሩ እንዲሰፋ ተጨባጭ ሥራዎች መሰራት ይጠበቅባቹሃል። በአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ፣ በመኢአድ፣ በኦፍዴን፣ በትግራይ አረና በመሳሰሉ ሰላማዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ በየክልሉ የሚደርሱ ወከባዎች በአስቸኳይ እንዲቆሙ መደረግ አለበት። በየክልሉ ላሉ አባሎቻቹህ ስልጠናና ጥብቅ መመሪያ በመስጠት የአገሪቷ ሕግ ከፌደራል ጀምሮ እስከ ቀበሌና ወረዳ መከበሩን ማረጋገጥ ይኖርባቹሃል።

- ቅንነት ችግሮችን ለመፍታት ቁልፍ ነገር ነዉ። ቅንነት ደግሞ ከመተዋወቅና ከመቀራረብ የሚመጣ ነዉ። የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ከማዋረድና ከማቅለል ይልቅ ከነርሱ ጋር መቀራረብና መግባባት እንዲኖር ሁኔታዎችን አመቻቹ። እንደ ወንድማማቾና እህትማማቾች አብራቹህ ቡና ጠጡ። አስባችሁት አታወቁ ይሆናል እንጂ ዉቂያኖስስ አቋርጠዉ ከሚመጡት ፈረንጆች ይልቅ የሚቀርቧቹህ እነርሱ ናቸዉ።

የተዋረዳቹህና እንደተሸነፋቹህ የምትቆጠሩ መስኪቹህ ከላይ የዘረዘርኩትን ለማድረግ ይከብዳቹህ ይሆናል። ነገር ግን ትልቅ ሰዉ እዋረዳለሁ ብሎ ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅምን ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም።።ግድ የለም ትላላቅ ሰዎች ሁኑ።

እንግዲህ ከስህተታቹህ ታርማቹህ፣ የሰላምንና የእርቅን ጥሪ ተቀብላቹህ ፣ የሕሊና እሥረኞችን ፈትታቹህ ለሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ሁኔታዎችን ታመቻቻላቹህ የሚለዉን ትንሿን ተስፋዩን ይዤ እጠባበቃለሁ። ምድርና ሰማይን የፈጠራ ተዓምረኛዉ አምላክም ይጨመርበት።